3-10-92

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ........................... | 1 |
| እስከመቼ ለሞት ደጅ ጥናት? ............ | 6 |
| ብዙአየሁ .......................... | 9 |
| የትግል ሠልፈኞች ...................... | 12 |
| በሽታው ምንድን ነው? ................. | 15 |
| ሕዝቡ ለሥልጣን በቃ ተባለልን .......... | 18 |
| በሕይወቴ ሥፍራ የያዝሽው ............. | 22 |
| ሰው`እምባሉን ፈርቶ ................. | 23 |
| ለፍቅር ፈቃድ ........................ | 25 |
| የወንድም ሞት ........................ | 27 |
| እናት ሕይወት ........................ | 28 |
| ሕልሜ ሳያልቅ ነቃሁ .................. | 30 |
| እውን ጦርነት ነፃነት ይሆን ........... | 31 |
| አደይ አበባ .......................... | 33 |
| ስደት ............................... | 34 |
| የካቲት ............................... | 36 |
| የትርምስ ሽግግር ...................... | 37 |
| የሚታፓኩ ግጥሞች .................... | 42 |

# መግቢያ

ግጥም፣ በተመረጡና በተሰኩ ጥቂት ቃላት ውስጣዊ የሰው ስሜት በፅሑፍም ሆነ በቃል የሚገለፅበት ዘይቤ ነው። ስለዚህም ግጥም የቃላት ጥርቅም ወይም የሚያማምሩ ቃላት የሚያሸበርቁበት የሥነ ፅሑፍ መግለጫ ሆኖ መታየት የለበትም። ግጥም፣ የግል ውስጣዊ ስሜትና የዚህ ስሜት ምንጭ የሆኑት የማኅበራዊ ልምድና ኀሊና መግለጫ ነው። የግጥም ትልቅ ፀጋም ይኸው ውስጣዊ ስሜትን በተመረጡና በተሰኩ ጥቂት ቃላት አማካይነት በይፋ መግለጹ ላይ ነው። አንድ ባለቅኔ (ገጣሚ) ፍቅሩን፣ ብስጭቱን፣ ሀዘኑን፣ ትዝታውን፣ እድናቆቱን፣ መቆርቆሩን፣ እምቢተኛነቱን፣ ናፍቆቱን፣ ፀፀቱን፣ የመንፈስ ስብራቱን፣ ብቸኝነቱን፣ ቁጡነቱን ሁሉ በቃላት መጥኖ በግጥም አማካይነት ያስተላልፍበታል፤ ያበስርበታል፤ ያረዳበታል። በዚህም ፀጋው የተነሳ ግጥም፣ የገጣሚውን ብቻ ሳይሆን የብዙ ሰዎችን ስሜቶች፣ ማኅበራዊ ልምድና ኀሊና በጋራ የሚያስተሳልፍ ሆኖ ይገለፃል። ይህም በመሆኑ ነው በየግጥሙ የሚሰማው ባለአንደበት የግድ ገጣሚው ነው ብሎ ማለት የማይቻለው። አቅራቢው ገጣሚው ይሁን እንጂ፣ የስሜቱና የልምዱ ተካፋዮች ብዙ ሰዎች እስከሆኑ ድረስ መልእክቱ ባለቅኔውን ብቻ የሚመለከት ነው ማለት ትክክል አይሆንም።

ግጥም፣ የአነባበብ ስልትና አያይዘም የግንዛቤ ልምድን ይጠይቃል። በዚህም ለመካን፣ ግጥሙ መቼ እንደተፃፈ መገንዘብን፣ የግጥሙ ልሣን ምን አይነት ባህርይ ባለው ሰው

ስለውበት የየራሳቸውን ልዩ ምርጫ ግጥሙ እንደ መስታወት ከሰያቸው፣ አንባቢዎች ከገጣሚው ጋር የስሜት ደባል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አንድ ማስረጃ ነው።

ከላይ ስለግጥም አነባበብና አገነዛዘብ ካቀረብኩት አጭር ማስታወሻ በተጨማሪ፣ ስለአገጣጠም መንደርደሪያ የሚሆኑ ጥቂት ነጥቦች ከራሴ መጠነኛ ልምድ ማስታወሱ ጠቃሚ ይመስለኛል።

1) ግጥም፣ ቤት እንዲመታ ሲባል ከመነሻ መድረሻ ቃላትን ለዚሁ መምረጥና ማሰናዳት የማያፈናፍን አቀራረብ ነው፤ ከመልእክቱ ያዘናጋል፤ ፍሬ ከርስኪ ቃላትን ያግበሰብሳል። ስለዚህ፣ በየስንኙ መተሳሰፍ ይገባዋል የምንለውን የመልእክቱን ፍሬ ነገሮች ለመነሻ በነጥብ መልክ ማስፈር።

2) ለተመረጠው መልእክት ፍሬ ነገር ማስተሳሰፊያ ሁነኛ የሚባሉ ቃላትን ማጠንጠን፤ በቅደም ተከተል አሰካካቸውን ማቀናጀት፤ አግረ መንገድንም ቤት እንዲመቱና ለስንኞቹ የአቀራረብ ቅርፅ እንዲይዙለት ማሰናዳት።

3) መላልሶ ማንበብ፤ የተመረጡ ቃላትን እንደገና ከተቻለ በተሻሉ ቃላት ለመተካት መሞከር፤ አሰካካቸውን ይበልጥ ማሳመር፤ የየስንኙን አደራደር ቅርፅ መጠበቅ።

4) የቃላት ድግግሞሽን ማስቀረት፤ አለማንዛዛት፤ በአዝማችነት የሚደጋገም ስንኝ የመጠቀም የአገጣጠም ስልት ካልሆነ በቀር ግጥምን እጅግ አለማራዘም።



5) ታሰቅ የገጣሚነት መለኪያ ነው በሚል ፍቺአቸው ቀለል ያልሆኑና ለአንባቢ ግራ የሚያጋቡ ከባድ ቃላት አለማንጋጋት፤ ቅልልና አጥር ምጥን ባሉ ግሩጭ ቃላት መልእክቱን በሥዕላዊ መልክ መድረስ።

6) የገጣሚውን ስሜት ለመገንዘብ እንዲቻል በግጥሙም ርእስ ሆነ ግጥሙ የተደረሰበትን ቀንና ቦታ መግለፅ ለአንባቢ እንደ ፍንጭ ሆኖ ያገለግላል።

ጴጥሮስ ቶጃ

<u>ህዳር 1984</u>

## ክፍል አንድ

### እስከመቼ ለሞት ደጅ ጥናት

እናት ፍሬዎቿን አፍርታ
ለተፈጥሮ አደራ በቅታ
የእያቶቿን የዘር ፀጋ ጠብቃ
መጥውን ትውልድ ተከታ፣

የምድር ማኅፀን ግን መከና
እፍኝ እንኳን እህል ጠፍቶ
ወገን በሰቆቃ ተንኳቶ
ከሞት መንደር ተጠግቶ፣

እስከመቼ?
ወገን ረሃብ ደፍቶት
እካሉን አጠውል ጉት
በቆዳው አስቀርቶት
ያለእድሜው አኩራምቶት፣

ኧረ እስከመቼ?
ምድር ፍሬ ነፍጋ
ለአንድ እግር ቡቃያ ቀዳዳዋን ዘግታ
የሕይወት እስትንፋስ እምቃ አሽጋ
ለሞት ሲሆን ከርሷን ከፍታ፤

ወገኖች ትንሽ ተሰሩ ተመገበው
የሕይወት ጉዳና ሸተው
እንደ ህፃን የእንፉቅቅ ቧችረው
ከረሃብ ሊያመልጡ ረሃብን አዝለው፤

እስከመቼ?
ሠማይ ብራ ሆኖ ፈክቶ
ለወገን መርደ ሀዘ ኔታ አጥቶ
የደመና ከል ገፎ ጥሎ
በእንባ ፊቴን አለብሰም ብሎ፤

ንጥረ-ምግብ ከአንጀት ጠፍቶ
አካለ-ሥጋ የሚያልመው አጥቶ
የገዛ ህዋሱን እሳምጦ በልቶ
ወገን በአጥንቱ ላይ ቆዳ አጣፍቶ፤

እስከመቼ?
ወገናችን ትናንሽ ሞቶችን ሞቶ
በየሰዓቱ በሕይወትና በሞት መኻል ተንከራቶ
እስከአድማስ ጥግ ዙሪያ ገባውን ቃኝቶ
ለነፍስ ደራሽ ወገን አጥቶ፤



እስከመቼ?
ወገን ከሞት ደጃፍ ተሰልፎ
ተረከበኝ ብሎ ተማጥኖ፤
እስከመቼ?
ሞት እንኳን ጨክኖ
ደጅ እሰጠኝ ሆኖ፤

<u>ህዳር 1976</u>

## ብዙአየሁ

አንድ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ በጉንደር ክፍለ ሃገር ውስጥ በዓይኑ የተመለከተውን ሲገልፅ ስለእንዴት ብዙአየሁ የተሰኘች ህፃን ሁኔታ እኤአ ጁን 27፤ 1983 እንደሚከተለው ፅፎ ነበር:-- «ይህንን ፅሑፌን ገና በምታነቡበት ጊዜ ብዙአየሁ ተሰማ የተባለች በአጥንቷ የቀረች የሁለት አመት ህፃን ልጅ በሕይወት አትቆይ ይሆናል። ብዙአየሁን ጉንደር ክፍለ ሃገር ውስጥ ዝዊ ሐሙሲት በሚገኘው መጠለያ ጣቢያ ውስጥ በአየኋት ጊዜ አራት ተኩል ኪሎ ግራም ብቻ ስትመዝን ቁመቷም 60 ሴንቲ ሜትር ብቻ ነበር። አንድ የአሜሪካን ጤናማ ህፃን የርሷን ያህል ክብደት በተወለደች በወር ወይም በሁለት ወራት ትመዝናለች። የብዙአየሁ ጥቃቅን አጥንቶች በተጨማተረው ቆዳዋ ላይ ፈጠው ይታያሉ። ክንደቿም ሁለት የወጥ ማማሰያዎች ያህላሉ። መላው ሰውነቷና ዓይኖቿ በዝንቦች ተወረዋል። እናቷ እየተማጠነች ልታጠማት ብትሞክርም ከመዳከሟ የተነሳ ወተቱን መጉንጨት ባቃታትም ኩባያ ላይ ዝንቦች ሠፈረዋል።»

ብዙአየሁ ...
እንደህፃን እንኳን ጡት አልጠገብሽ
ውሀ ከጠፋበት ምድር መጥተሽ
እንደህፃን እንኳን አረ አላልሽ
ኃይል ጠፍቶ ትንፋሽ አጥሮሽ፤



እድሜሽ በቀን መቁጠሪያ ተሰልቶ
ሁለት አመት ተብሎ ተገምቶ
የአሳለፍሽው አልፍ ስቃይ ተዘንግቶ
የዝምታ ጠኔሽ በቸልታ ታይቶ፤

ብዙአየሁ ...
እውነትም ብዙ አየሽው
የስቃይ ወርዱን አቋረጥሽው
የሞትን ደጃፍ ጉበኘሽው
በብላቴና እድሜ ባልቴት ሆንሽው፤

ወላጅ እናትማ መች ጨከነች
በጣር ላይ ነው የከረመች
ታበላሽ የላት ተሳቀቀች
ብዙአየሁ ብላ በስም ካሰች፤

በወላጅ እናትሽ እቅፍ ላይ መሆንሽ
እንደዕድል ተቆጥሮ ዕድለኛ ሆነሽ
የእናት ጠረን ናፍቀው በንቺ በቀኑብሽ
ያለእናት በቀሩት ህፃናት ዓይን ታይተሽ፤

ብዙአየሁ ...
በምፅአት መኸል ተወልደሽ
በደመ-ነፍስ ግንዛቤሽ
መፈጠርሽ ገራ አጋብቶሽ
የሕይወት ፍቾው ውሉ ጠፍቶሽ፤

ረሃብ ጠርቦ አስለምልሞ
በቆዳ በአጥንትሽ አቁሞ
በህያው ሙትነት መሰሎ
ነፍስ አባትሽ ሞት ነው ብሎ፤

<u>ግንቦት 1975</u>



<u>የትግል ሠልፈኞች</u>

ብርሃን ጨለማን ሲተካ
ወገግ ሲል ብልጭታ
ተፈጥሮ ጥቁር ሸማዋን ጥላ
እውን አካሏን እዩት ብላ፣

ደብዘዝ ባለው ሠማይ
ጭጋግ በሸፈነው አየር
ከፉፆ ባራሰው ምድር
ውርጭ በ ጉበኘው አገር፤

በአገር አሜሪካ
በ ኒውዮርክ ከተማ
ሠማይን ህንፃ ደግፎት
ምሰሶ እውታር ሆኖት፤

ወገን ወዳድ በሠልፍ ተራ ቆሞ
ትከሻ ለትከሻ ገጥሞ
የልብ ትርታውን አመጣጥኖ
በህብረት ትግል አስገምግሞ፤

ሠሊዳዎችን አንግበው
ወገዛውን ፈክረው
«ኢትዮጵያን ተውልን
ክብራችንን መልሱልን!

«እምባገነንነትን እምቢ
ዲሞክራሲን እሺ!»

ሠልፈኞች በሠልፍ ተራ ቆመው
ደርግን፣ ራሺያን ኮንነው
«ወጊድ ብለው ያንን አስመሰይ
የህዝብ... የአገር ተባይ!»

አገር ወዳድ በሠልፍ ተራ ቆሞ
ትከሻ ለትከሻ ገጥሞ
የልብ ትርታውን አመጣጥኖ
በህብረት ትግል አስገምግሞ፣

ሠሌዶችን አንግበው
ወገዛውን ፈክረው
«ኩባዎች ከአገር ውጡ!
ራሺያኖች ጣልቃ አትግቡ!»



«ዴሞክራሲ ይለምልም!
እምባገነንነት ይውደም!»

የወገን ወዳድ ልሣን ተከፍቶ
ዲዳ አልሆንኩም አለሁ ብሎ
የትግል ዜማውን አሰምቶ
የትግል ተሃድሶውን አስመስክሮ፣
«አትነሳም ወይ አትነሽም ወይ?
የሕዝብ ወገኖች አይደለችሁም ወይ?
ለዴሞክራሲ ለነፃነት አትታገሉም ወይ?
ተነስ! ተነሽ!»

መፈክሩ ዜማው ተሰተጋብቶ
ከህንፃ ህንፃ ተላግቶ
የታጋይን ወኔ አገያይቶ
ብሩህ ተስፋን ዘርቶ፤

ጥ ቅምት 1976

<u>በሽታው ምንድን ነው?</u>

በልቼ እየጠገብኩ ረሃብ ይሰማኛል
ጠጥቼ እየረካሁ እጅግ ይጠማኛል
ስቄም ተጫውቼ ሃዘን ይገባኛል
ስም የለሽ በሽታ ይዞ ጧምድዶኛል፣
ከሰውም ጋር ሆኜ ብቸኛ እንደሆንኩኝ
በቀዝቃዛ ስሜት ምናኔ እንደሄድኩኝ
ህዋ ውስጥ እንደሆንኩ በመንፈስ ስወራጭ
ምንግዜም ሽልብታ በቁሜ ሸፍኖኝ፤

በረድ ያለ ለታ ሙቀቱን ስመኘው
ሙቀቱም ሲመጣ ብርዱን ስናፍቀው
የታመቀም አየር ሰንበየን ሲያቆስለው
ትንፋሼ መቆሙን እንደፈውስ ልቆጥረው፣

ከሃገር ርቆ መንጉዱ
ከዘመድ ከወገን መነጠሉ
ሃሣብ ለሁለት መከፈሉ
በአንዴ ሁለት ቦታ መኖሩ፣

በሽታው ምንድን ነው?
የጭንቀት ምርኩኛ የሚያደርገው
የሰቀቀን ወረርሽኝ የሚያዘምተው
ልብን ለሁለት የሚገምሰው፣



ትዝታ ነው? ናፍቆት?
ፈረንጆች «ኖስታልጅያ» የሚሉት
ወይስ የነፃነት ጥማት?
የሰብአዊ መብት እርዛት?

ባእድ ደዳም አልሆንኩ ልሳኔ ክፍት ነው
የእንግሊዝ ቋንቋውን እሞክክራለሁ
ግና - ለወሬው ለቀልዱ ለዛ አጥቻለሁ
ከወገኔ እንደበት ለዛ አጣጥማለሁ፤

ሥነ-ልቡናው ልዩ ባህሪው ለየቅል
በግል መሯሯጡ ለራስ ብቻ መኖር
ምንቸገረኝነት ፋፍቶ .... መተሳሰብ ከስቶ
ከሌላው ተጋርዶ የግልን ሆድ ሞልቶ፤

በሽታው ምንድን ነው?
የጭንቀት ምርኩኛ የሚያደርገው
የሰቀቀን ወረርሽኝ የሚያዘምተው
ልብን ለሁለት የሚገምሰው፣
ትዝታ ነው? ናፍቆት?
ፈረንጆች «ኖስታልጅያ» የሚሉት
ወይስ የነፃነት ጥማት?
የሰብአዊ መብት እርዛት?

የዜግነቴ መብት ታውቆልኝ ተከብሮ
ነፃ ሠላም ሆኜ መኖር ብችል ኖሮ፣
በሽታው ሊለቀኝ ላያ ኩማትረኝ
የሰቀቀን ቀለብ ከመሆን ሊሻለኝ፤

ታዲያ .....
እርቄም ሳስበው ናፍቆቴን ልወጣው
የወገኔን ኑሮ ደስታውን ስመኘው
እርሱም እንደ እኔው .....
ኑሮው በሰቀቀን...ሰቀቀን ኑሮው ነው
ሠላም ... ነፃነት አጥቶ
ጨለማው እንዲነጋ ብርሃን ናፋቂ ነው።

ህዳር 1978



## ሕዝቡ ለሥልጣን በቃ ተባለልን

የዲሞክራሲ ቃና ተለውጦ
በጥራዝ ነጠቆች ገልምቶ
የተበሩ ፅንሱ ሟሽቶ
ቀሮ ቃልነቱ ቀርቶ

ምርጫ ብለው እደናግረው
አጋፋሪዎቻቸውን እንደሸን ጉ ወታትፈው
ካልኖሩበት ለማያውቁት ቀበሌ ታጭተው
በእጅ ተለቃቅመው በቀን ተነፍሰው

የሕፃን ጨዋታ ማውገርገር
ምርጫ ብሎ መሸንገል
አጭው... ታጭው
አንድ አምባል አንድ አከል
«ታሪክ» ነው..
ያልታየ ታሪክ ነው ተባለልን

ሳይለውጥ ማንነቱን
የእምባገነን ምግባሩን
እዚያው በዚያው ሙልፎ ሹመቱን
ከሊቀ መንበርነት ፕሬዚደንትነቱን
የምሥራች ተባለልን
ጉድ ነገር... «የሕዝብ ሥልጣን»

ዘንድሮማ ተከነው በቅጥፈቱ
ተረዘዝመው ከጊዜያዊነት ወደቋሚነቱ
ተንፈራጠው በሥልጣን ሠገነቱ
ሕዝባውያን ተብለው ሲሠርጉ

የቅጥፈት መጉናጠፊያውን አጥልቀው
በግፍ በማንአለብኝነት ጥዋ ተሰክረው
የተሜ ኑትን ሕዝብ ለሥልጣን በቃ ብለው
የጊዜ አብቶች ተሸለልመው
በሊቀ-አስመሳያቸው ተባርከው

እዚኝ መሰይ ቅቤ አንጊቾች
የውስጥም አስተዳደር አርቃቂዎች
አገር አተራማሽ አመሰቃይ መሐንዲሶች
ሕዝብ እንከራታች የግፍ አውጠንጣኞች



የምርጫ የዲሞክራሲ ለዛ ትርጉም በኖ
የእመስ-ጥፉው ሁሉ ማጋጌጫ ሆኖ
በርኩሱን እንደ ድርሣኑ-ሥልጣን ተደግሞ
እንደመሰንበቺያ ግዝት መሃሰ ተቀንቅኖ

የሃዘን ጉም እንዲለዘመመ
መርደ በየቤቱ እንዳልተከረመ
ለእለት ጉርስ እህል እንዳልተቃረመ
የየከቲት ተበፋ ጨረር እንዳልተጫሰመ

የደስታ አገር ነው ተባለልን
ብልፅግና በልፋፊ ተነገረን
የተሰፋ እሸት መጉርሚቱ ተበሰረን
«የሕዝብ ሥልጣንም» ተዘከረን

የዲሞክራሲ ቃና ተለውጦ
በጥራዝ ነጠቆች ገልምቶ
የትስፋ ፅንሱ ሟሽቶ
ቀፎ ቃልነቱ ቀርቶ

ከመተዳደሪያ ሥርዓትነቱ
መለፈፊያ እስመሰይነቱ፣

ከሕዝብ መብት መገልገያነቱ
ማሰዘኚያ እልኩ በይነቱ፣

በፅሑፍ በድርጅት ነፃነት ከመገለጡ
በታንክ መከከቱ
እንደበሩድ በብረት መወቀጡ
በማንአለብኝነት መሰቆጡ

የወገን ልሣን እንዳያደምፅ ታፍኖ
ውዳሴ-መንግሥቱን ብቻ
 እንዲደግም ተበይኖ
እንደልቡ እንዳይዘዋወር
 ወገን እግሩ ተሰንክሎ
ምርጫው ነፃ ነው ተባለልን
 ተሿሚው ከበፊቱ ተወስኖ፤

<u>መስከረም 1980</u>



<u>በሕይወቴ ሥፍራ የያዝሽው</u>

አንቺን ደግሞ ምን ይሉሽ
መለኮታዊ ሥልጣን አልተሰጠሽ
ሳላልምሽ ..... ሳላስብሽ
ነጠላነቴን ተጋፍተሽ
በሕይወቴ ሥፍራ የያዝሽ፤

ደርሰሽ ብቅ ብለሽ በዓመት መባቻ
ሳላቅደው ሳልዘጋጅ ላንቺ እውቂያ
በሕይወት ጉዞየ ላይ ድቅን ያልሽው
ልቤን በደስ ጉዳና ያስቀየስሽው
ነጠላ ሕይወቴን በጥምር የተካሽው
ለሕይወቴ መዓዛ ከጣዕም የሰጠሽው፤

እምቡጥ የፍቅር ዝከርሽን ቀማምሼ
በማርያም ፅዋ አምሳል እማኝነቴን ገልጬ
ወር ሳልጠብቅ በየሣምንቱ ተሳልሜ
ስምሽን ትዝታሽን እንደአልባስ በልቤ ጥምጥሜ
ልፋፊ ፍቅርን በእጥፍ ቁመቴ ልክ ጠቋቁሜ
ከእንግዲህ አንቺው ነሽ የሕይወቴ ልምሳሜ፤

<u>ጥቅምት 1982</u>
(ለዘውድነሽ ዘገዬ)

<u>ሰው እምሰሉን ፈርቶ</u>

ከጅማሬው ሰው በነጠላ አልነበረ
ለብቻው አልኖረ
ሕይወቱ ማኅበራዊ በጋራ የዳበረ
የትውልድ ዘርፉን ያስከበረ፤
ግላዊነቱ ፍች የለው
ሕላዌ አይሰጠው
<u>እኔ</u> ብሎ አያኖረው
ከጥቃት አይጠብቀው፤
ማኅበረ- ሰብእ ነው የሰው ሰውነቱ
ማንነቱ...የትውልድ ፅናቱ
የባህሉ... የታሪኩ... የሥልጣኔው ርስቱ
የህልውናው ምንጭ እትብቱ፤

ሰው ከሰው መመሳሰሉ ቀርቶ
የእምሰልነት ጥቅል ባህሪው ጠፍቶ
አንዱ ከአንዱ ሲለያይ ፍላጐቱ ተለዋውጦ
ማኅበራዊ እኩያነት ተገልብጦ
በድሎትና በእጦት ተቆራርጦ፤
ከማኅበራዊ ማኅፀኑ አይመነጠቅ...አይወጣ
በነጠላ ፍሬነት የሕይወት ዘር እያመጣ
ጥቅል ሰብእነቱን ደምስሶ እያጠፋ
ህልውናው በማኅበር እንቀልባ ተታቅፋ፤



ዘመኑ.. ዘመነ ግልምቢጦሽ ሆኖ
ግለሰቡ በማኅበረ-ሰብእ ተከድኖ
በየራሱም ቃዘ ተከልሎ ተሸፍኖ
ሕይወቱን ሲያተርፍ ከመሰሉ መንኖ፤
የእኗኗር ግጭት ....
የጥቅም መጓት ....
ተራና ረቂቅ ስርቆት....
ተጋድሎ ፍጅት....
ሆነውት የዕለት ኑሮው ተውኔት
የሰው ልጅ ሰውን ፈርቶት
ውሎ-ገባ በዐይነ ቁራኛ ተጠባብቆት
ሳይቀደም .... ሲቀድም .... ሲዘራከት።

<u>ጥቅምት 1982</u>

## ለፍቅር ፈቃድ

እድሜና ዘመኑ ፈቅዶማ ቢሆን
እይኑ አፋርነቱ ባልከፋም ነበር
በጊዜ ወንበር ላይ ቁጭ ብለን አውግተን
እጅ ለእጅ ተያይዘን ወራቱን በቆጠርን፤
ክረምትና በጋን አብረን ባፈራረቅን
የመሬትን ዙረት መርምረን በሰላን፤

እድሜማ ቢኖረን ...
የአባይ ፈሰሱን መሰልሰን ባየነው
የአዋሽ መድረሻውን ቀርበን በቃኘነው
ለማይዳሰስ ሰማይ ምሰሶ ስሆነው
የደጀንን ጋራ ሽቅብ በወጣነው፤

እድሜማ ቢኖረን ...
በሕር ዳርም እንሂድ በፍቅር ተማርከን
ማዕበሉ ያሸሸን ነፋሱም ይዳሰን
በረሃም እንግባ ንዳዱ ያቃጥለን
እደጋም እንውጣ ብርዱ ያንዘፍዝፈን፤



እንደማቀብሰላ እድሜማ ከገኘሁ
ለዓይኖችሽ ውዳሴ መቶ አመት ባጠፋሁ
ለጥርሶችስ ውበት ሁለት መቶ ልሰጠው
ለተቀረውማ እልፍም ላይበቃኝ ነው
ላንቺ ለውቢቱ ይኸውም ሲያንስሽ ነው፤

ከወደጀርባዬ ድምፅ ይሰማኛል
የእድሜ ሠረገላ ይበራል ይከንፋል
ከእድሜየ ወሰን ላይ ተጠግቶብኛል
እሰፍሮ ሊወስደኝ እጅጉን ተቃርቧል፤

እኔም ከተሰናበትኩ እድናቂሽ ልለይሽ
ጊዜም ውበትሽን ተራምዶት ሊያልፍብሽ፤

ጊዜው አሁን ከለን እንፈቃቀድበት
እድሜ በፊታችን ሳይራመድበት
በለጋው ቀዳችን ትልም ሳያወጣበት
በራሳችን ፀጉር ጥጥ ሳይዘራበት፤

እንደተቀናጁ የፍቅር እርግቦች
በአየር ላይ እንብረር በየብስ እንበራች፤
መድረሻን ይሁን ሰባተኛው ሠማይ
በእካል ተለጣጥቀን በስሜት በአንድ ላይ፤

ታኅሣሥ 1981

**<u>የወንድም ሞት</u>**

ለስድስት እመት መለየትህ
ገና..ትናንት ሲመስለን አስታውሰንህ
ዛሬ ለአፍታ ዘወር እንዳልክ ሁሉ ስናስብህ
በልባችን ተከድኖ የማይጠፋ ትዝታህ፣
ሞት ግርደሹን ጥሎ
ውድ ወንድምን አርቆ ከልሎ፣

እንዳያስረሳን .....
ቀምነገርህ መች ተዘንግቶ
አይዘነጋው ፍቅርህ እንዴት ተመክቶ፣

እንዳያራርቀን .....
መንፈስህ በሰውነታችን ጠልቶ
አልሄድ አለ ተለይቶ ርቆ፣

<u>አረፍክ</u> እንዳንልህ
መች አረፍት ሰጠንህ
ስምህን እየጠራን፣ እያሰብንህ
በአምሳል ልጆችህ እያየንህ፤

<u>የካቲት 1982</u>
(ለበእምነት ዘገዬ)



**<u>እናት ሕይወት</u>**

ከፍሬሽ ትሩፋት ዘግነሽኝ
የሕይወት እስትንፋስ ሰጥተሽኝ
ከምንም-ነት <u>ለሰው</u>ነት አብቅተሽኝ
የዉ ቅላ የጎልማሳ ዘመን አራመድሽኝ፤

የፍጥረቴ የብቃቴ መሐንዲስ
ከላንቺ ምን ልደርስ
ከየት -- ወዴት ልሳወስ
ባታስቢኝ ባታምጭኝ ከየት ልፈልስ፤

ጡት ጠብቼ
ኃይልሽን ተሸምቼ
በአንቺው ጉልብቼ
በእካል በርትቼ፤

አንቺ ተርበሽ
እኔን አስቀድመሽ
አጉርሰሽ አጥግበሽ
ጠግቢል ሳትይ ተሰቀሽ፤

በአብራክሽ ላይ ልሣኔ ተፍታቶ
ባ..ባ ማ..ማ ን እጥንቶ
በአንቺው ድጋፍ ፊደል ቆጥሮ
ኅሊናየ በስሎ አእምሮየ ተመራምሮ።

ለማልጨ ነቅበት ለኔው ኑሮ
ስለእኔ ያንቺው ጭንቀት ሆኖ
ልብሽ ሁሌ ተብከንክኖ
የሰቀቀን ፍም ከድኖ።

«የወላጅ ጭንቀት
ልጅ መች ገብቶት
ወልደው እስኪያዩት
በተራቸው እስኪቀምሱት»

ብለሽ የምትይኝ
አስገንዝበሽ የምትነግሪኝ
የፍቺው ስሜት ሲጠፋኝ
የወላጅነት ተራው እስኪደርሰኝ።

<u>ጥር 1983</u>
(ለወ/ሮ ዳሪቱ ፋንታ)



<u>ህልሜ ሰያልቅ ነቃሁ</u>

በትንሽ ሞትነት ባህሪው
እንቅልፍ አካሌን ሲያሰርፈው፤
በህልም ፍኖት ተንሰፍፌ ተምሜ
ከውብ አለም ልደርስ አስገምግሜ።

ጥጋብ እንጂ ረሃብ ከሌለበት
ከደስታ በቀር ሀዘን ከማይታወቅበት
የማኅበራዊ እቻነት ሚዛን ተደላድሎ ከቆመበት
እነስስት ..ክፋት ..ጥላቻ ቤት ካልሠሩበት
እደርሳለሁ ... እኖራለሁ ብየ ስዋትት።

በህልም ጉዞ ተሽመድምጄ
አካሌ ሲድህ በላብ ተጨፍቄ
ህልም ሆኖብኝ ተስፋ ይዞኝ
እምነት አፅንቶኝ እንደርድሮኝ
ስንዝር ሳልሄድ የቀረብኩ መስሎኝ
ካሁን ካሁን ደረስኩ ስል ብንን አልኩኝ
ከጣፋጩ ህልሜ ተለየሁኝ።

<u>ግንቦት 1982</u>

## <u>እውን ጦርነት ነፃነት ይሆን?</u>

ለነፃነቱ ከሚተኩስ ጥይት ሸሽቶ
ሌት ሌት የደረጉት እህል ዘክሮ
ከሌት ወፍ ጋር ተጋፍቶ
በዋሻ ደባልነት ገብቶ
ሲነጋ ተደብቆ
እንበቃቅላውን* ይዞ
ዱር ተሸሸጉ፤

ሠላም አገኝ ብሎ ተስፋውን አዝሎ
የነፃነት ውጋጋን ደረሰ ሲል
ጦርነቱ ያባራ ይመስል
ጦርነት ጦርነት እያጋጋለ
ባሩድ እየዘራ
ሕይወት እየቀጠፈ
ስቃይ.. ስደት.. እያበራየ
ወገን ከወገኑ እነካክሶ እየለየ
ምስል እኩልነቱን እራርቆ
በመኖሪያ ቀየው መለያውን እስጠብቆ፤

---

* ሕፃናት ማለት ነው።



በዚህም በዚያ መለያው ተደንግጉለት
ማሳሰቢያ ጦር በሰሙ ተሰብቆለት፣
ከዚህም .. ከዚያ ጦር ተዘክሮለት
የመቀራረሚው ጉዳና ተደንግጉለት፤

በእውን ጦርነት ...
ሠላም.. ሕይወት ይሰጠው?
የብረት ክምር እድገት ይሆነው?
መለየቱ ነፃነት ይወጣው?
እንድነቱ ለነፃነት ያበቃው?

እነደዘመኑ-መሣፍንት
የጦር ባህል በሚያኩራበት
ህግ ሆኖ በሚደኝበት
ጉልበት አእምሮን በሚመራበት
ድል ማለት...
የሰው ግዳይ መጣል በሆነበት
አይ.. ነፃነት ተብሎ ነፃነት
ሕዝብ በማይከበርበት
ድምፁ በማይሰማበት
በዚህም .. በዚያ
አውቅልኸለሁ በሚባልበት፤

<u>ግንቦት 21፣1982</u>
(ለምፅዋ ነዋሪዎች)

## <u>አደይ አበባ</u>

አደይ አበባ
ምንጊዜም አደይ አበባ
የአዲስ አመት አርማ
የዘመን መግቢያ
የትንቢት ተስፋ።

ሰንሰሉም አደይ አበባ ሲባል
ሙጃ ቀልቋሉም ሳይቀር
ከአደይ አበባ ዘር ሲቋጠር
ካልፈራበት ካልሆነበት ሲደነገር
በስም ውስት ባህሪውን ሲያዘውር
መልክና ጠረኑን ይተው ይመስል።

<u>መስከረም 2፤1976</u>



## <u>ስደት</u>

ግፍ በደል ሲከመር
ጭቆና ሲሞሸር
ትንፋሽ ቁርጥ ሲል
ሕይወት አቀፎ መብረር።

ስደት ብሎ ነገር
ጊዚያዊ ውሳኔ ሲወጡ ከአገር
ቀን እስኪያልፍ ዘወር
ጭለማ እስኪነጋ ሰወር ሰወርወር።

«አገሬ ቢስ» ብለው መለያ ሲሰጡኝ
ተባራሪ-ወፍ ነህ ብለው ሲሰይሙኝ
ዜግነት እንዳለኝ ሲያጠያይቁኝ
ምድቤ ጠፍቷቸው <u>ማንነት</u> ሊቸሩኝ።

ኢትዮጵያዊ .. በኢትዮጵያዊነቴ
የአእላፍ እመታት ትውልድ መሠረቴ
ታሪኳ.. ባህሏ.. ቅርሴ ምስክሬ
ኩሩ ወገኖቼ የማንነት ምስሌ።

በደት ፈታተነኝ ጉልበቴን ሲለካው
የትግሥቴን መጠን በጊዜ ሲሰፍረው
የመንፈሴን ፅናት በኑሮ ሲፍቀው
ልኬን አሰንሼ እጄን እንድሰጠው፤

መንግሥትማ ጠፈ
የታሪክ ጎሰፈ...

የምሁሩን ልሣን እርግብግቢት ከድኖ
የጠቢባንን እጅ ገንዘ ከፍኖ
የሊቃውንት አእምሮ እንዲዝግ በይኖ
በጀ ያሰለውን ከሩቁ አግልሎ፤

አገር መች አጣሁኝ
መንግሥት መሰው ጠፋኝ፤

<u>ግንቦት 1983</u>



<u>የካቲት</u>

መስከረም በጠባ ጳጉሜ በወጣ ቁጥር
ግፍና በደሉ ሲጫን ሲደማመር
ነፃነት ሲዳመጥ ጭቆና ሲሞሸር
የካቲት አገድሽው የወሮቹ ደፋር፤

የካቲት ...

የታመቀ ትንፋሽ በአንቺ ተተንፍሶ
የተሰነከለ እግር ድንበሩን አዳርሶ
ታሪክ ቁጠሪ አለ ባንቺ ተመርኩዞ
እንድ አለህ በይለት ለወደፊቱ ጉዞ፤

<u>የካቲት 1974</u>

## <u>የትርምስ ሽግግር</u>

በጊዜያዊ ስም ሽግግር መጥቶ
ባለጦር ሄዶ ሌላ ባለጦር ተተክቶ
አእምሮ በጡንቻ ተገዝቶ
የአስተዳደር ውሉ ጠፍቶ፤

አይ! አስተዳደር ተብሎ አስተዳደር
በማያውቁት በማያውቃቸው መደናበር
መገንባትን ሳያውቁ ለማፍረስ መሽቀዳደም
ሠላም ሲፋለስ በሠላም ስም፤

የኢትዮጵያዊነት መለያው ተሸሮ
በየብሔሩ እንዲከተት ተነግሮ
ከፊሉ ከትውልድ ቀዬው ተገፍትሮ
ጋብቻ ያጣመረው እንደእርኩስ ተባሮ፤

የመገነጣጠያውን መቅደስ አንፀውት
በየብሔሩ እንዲከለል ገዝተውት
የጋራ አውድማውን ቆፍረውት
የታሪክ ቅርሱን ፍቀውት፤



የዘመናት ታሪኩ የተረት ያህል ባከኖ
ኢትዮጵያዊ ባህርይ እንደህልም ተቆጥሮ
በየብሔሩ እንዲሸጋሸግ ተወስኖ
አዲስ ታሪክ 'ሀ' ብለህ ጀምር ተብሎ፤

በጊዜያዊ ስም ሽግግር መጥቶ
ባለጦር ሄዶ ሌላ ባለጦር ተተክቶ
አእምሮ በጡንቻ ተገዝቶ
የአስተዳደር ውሉ ጠፍቶ፤

የአውቅልኽለሁ አስተዳደር ፅንስ
እንደወትሮው ሃገር ሲያተራምስ
የሠላም ቃል በደም ሲፃፍ
ዲሞክራሲው ብረት ሲለብስ፤

እንደወትሮው መንግሥት
የጉልበተኛ የወሬ ቋት
ተቃዋሚውን ማጥለስት
እንደጠላት ማሰጣት፤

እናት ኢትዮጵያ ተቀስፋ እንዳልተቀሰፈች
በጦርነት ምድጃ እንዳልተጣደች
ልጆቿን በሞት በስደት በእስራት እንዳላጣች
የሠላም የእርጋታን ተስፋ እንዳላማጠች፤

ወገን የእፎይታ ትንፋሹን ሳይወርስ
ገና ካሁኑ ምድሩ በብሬት ሲታመስ
አየሩ ሲታጠን በባሩድ ጢስ
ለጋ ሕይወት ያለፍርድ ሲቀነጠስ፤

ስንቱ ታፍሶ ታሠረ
ያለመጠለያ ያለምግብ በአጥር ታጉረ
እስኪጣራ ፍርድህ ስቃይህ ነው ተባለ
መሪር «ርኅራኄ» ከመሪዎቹ ተቸረ፤

መተኪያው ሳይሰናዳ ሳይደርስ
እስከዚያው ሁሉም ሲፈራርስ
አስተዳደር ሲተራመስ
ሃገር ሲቆራረስ፣

ተቋሞች ሲናዱ
መብቶች ሲታገዱ
ሕዝቦች ሲነዱ
ለሹሞች እንዲሰግዱ፤

ብረት ዳግመኛ ታቦት ሆነ
አምልኩብኝ ብሎ ወሰነ
ተክለ-ሰውነት ተመልሶ ገነነ
ባህታዊ መሪ ከጫካ ገቡ ተባለ፤



በጊዜያዊ ስም ሽግግር መጥቶ
ባለጦር ሄዶ ሌላ ባለጦር ተተክቶ
አእምሮ በጡንቻ ተገዝቶ
የአስተዳደር ውሉ ጠፍቶ፤

ጉልበት ሆነ የመሪነት መደንገጊያው
ቁልፉ የአስተዳደር መፍቻው
ቁምነገሩ የሥልጣን መከፋፈያው
እንደጥንቱ ኃይል ሆነ መከበሪያው፤

ከጀርባ ያልተኰለኰለው
እንደመናፍቅ የታገደው
ዴሞክራሲ የተነፈገው
የአማራጭ ድምጹ የታሸገው፣

ማረኝ እንዲል ተጠብቆ
ለዲሞክራሲ ምስክርነት ተጠይቆ
እምቢ ካለ እንዳይደርስ ተገዝቶ
እንዳይቀርብ ከሩቁ ተገፍቶ፤

ዴሞክራሲ ጉድ የጉድ ልጅ ሆነ
በግርግር ተጠፍጥፎ በብሬት ተከደነ
ማደነቂያ ብቻ እንዲሆን ተበየነ
ስሙ እንጂ ግብሩ በባሩድ እሳት ተነነ፤

<u>ጥቅምት 1984</u>

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሚታፕኩ ግጥሞች</u>

***

መሰልሺም ከፍቼ ዘግቼ
ለውጥ አላይ አልኩኝ ባይኖቼ
የድርው ተገልብጦ
ግልበጡ ተቀምጦ፤

* * *

ውሎ አድሯል እሉ ዳበውም ተደፍቶ
ባለሙያው ሳይገድ መመከከር ጠፍቶ፤

* * *

ታላቅ የሚል ስም ለራሱ ሰጥቶ
በጊዜ ሚዛን መለኪቱን ዘንግቶ
ከፍ-ዝቅ እንደሚል አላስተውል ብሎ
ጊዜው ሲደርስ ትንሽነቱን በኃፍረት ተቀብሎ፤

* * *

ነፃነት መግፈፊያ ቢሳ ካቀበሉ
ኃያል ባእድ ጋብዘው በገር ካሠፈሩ
መብት መደመጫ ብረት ከከመሩ
ከዚህ ሌሳ ለገር ምንድነው በደሉ?

* * *

የበረሀ ነፋስ የከመረው
የአሸዋ ክምር የተቆለለው
የቱን ደከማ ውጦት ይሆን?
የማን መቃብር ይሆን?

* * *

እንደበረሃ አሸዋ ደረቅ አፈር
በእጄ ዘግኜ ባሻሸው
ለራሱ በድን እርጥበት የሌለው
እንዴት ለሌላው ሕይወት ሊሰጥ ነው?

* * *



የመቶ አመት እንቅልፍ እንደተኛሁ
አዘግቼ ከሽልብታየ ነቃሁ
እንደት ሃሣብ ሳልይዝ ለትውስታ
ለካስ ጊዜው ቀን ሆኗል ማታ፤

* * *

ከወዲያ ወዲህ ስመለከት
ሰው ፍለጋ ስዋትት
በዚህ ስሰብር በዚያ ስወርድ
ለካስ የተጓዝኩት በማላውቀው መንገድ፤

* * *

በመንገድ ላይ ባለፍኩ ቁጥር
የማየው አንድ ሰው ለዘወትር
ኩርምት ብሎ ተጠቅሎ በድሪቶው
ዛሬስ ምነው ጠፋብኝ ያለወትሮው፤

* * *

ከእውቶብስ ጣቢያ የደረስኩ ሲመስለኝ
ተቀባይም ማረፊያም አጣሁኝ
ብቸኝነት የሞት ያህል ሆኖብኝ
በህልሜ ይሆን ብዬ ተመኘሁኝ፤

* * *

ኑሮ ኑሮ ብሎ ነገር የሌጣ ምሥጢር
በዘልማድ ትርጉም እንዲያው መውተርተር
ዝንበር ወጥታ ስትጠልቅ ሂሣቧን መቁጠር
እድሜየ ይህን ያክል ብሎ መተመን፤

* * *

ደስታ አገኝ መስሎኝ
ሠራሁኝ ባተልኩኝ
በተጠያቂነት እጆቼን አየሁኝ
እነርሱ ይሆን የነፈጉኝ?

* * *

ውብ ኩረዳ ወጣት
ባለሙሉ ስጋ ሕይወት
ስታወራ ሰማኋት
ስለሞት ስለኅልፈት

* * *



ፍቅር ያዘኝ
ተዋወቅሁኝ
ተጠጋሁኝ
ተቃቀፍኩኝ
ግን....
ለምን ሃሣብ ገባኝ?

* * *

ትዝ ሲለኝ
በጭለማ የተኛሁኝ
ያለውጋጋን ነቃሁኝ
ይንጋ አይንጋ አሰሰበኝ፤

* * *

ባንደርስ ከቤታችን
ጊዜው ጨለመ በጉዟአችን
እናጥፋው በገዛ እጃችን
ቀሪው ጭለንጭሉን
የአእምሮ ብርሃናችንን፤

* * *

ተስፋ ሰደርግ ለሠላም ፍኖቶች
የተቀየሱት የሃዘን መንገዶች
እንደቀድሞዎቹ ጎዳናዎች
እርምጃና እድገት አደናቃፊዎች፤

* * *

ስለነገው ተስፋ አለኝ በተበሩ
እምነቴን ስገልፀው በይፋ
ቃሌ ዋሸ አይሆንም
ግን ....ቢሆንም?

* * *

ነገ ይሸሳል ብዬ በተበፋ
ተኛሁኝ.. ለነገው ጉዞ ሳንቀሳፋ፤

* * *

የሰሳ ጎሊና እምቢ-ባይ ወቃሽ
የእግራጩን መቅረዝ ጫሪና ለኳሽ፤

* * *



ለፍቅር የሞቱ በፍቅር
ገድላቸው ይዘርዘር
ስማቸው በታሪክ ይሰፈር፣
በሰሠላም የሞቱ በሠላም
መታሰቢያቸው ይቁም
ለትውልድ አብነት ይሁን፤

* * *

ሰሚ ሳጣ ፀሎቴ
መልስ ለሌለው ምኞቴ
ከንቱ መልፋቴ
ለማሳውቀው እምነቴ፤

* * *

ትናንት.. ዛሬ..ነበር
ዛሬም .. ትናንት ሊሆን
ነገም ..ዛሬና ትናንት ሲሆን
ጊዜ ... ሲያልፍ
ስንቱ... ያልፍ፤

* * *

ለእውነት ቆምኩኝ
ለእውነት ተሟገትኩኝ
ላፍታ ግን አሰብኩኝ
በዋሾዎች መኻል ከንቱ ባዘንኩኝ፤

* * *

ይገርማል!...
ሠማይ ሳይታየኝ
ትዝ ሳይለኝ
ደርዘን አመት አለፈኝ፤

* * *

በብረት አጥር ውስጥ ተቀምጬ
የፖሊስ ጠባቂ ተመልክቼ
ደህንነቴ የተጠበቀ መስሎኝ
በወህኒ ሠላም ተደሰትኩኝ
ከውጭ ለሚጉላሉት አዘንኩኝ፤

* * *



ቅርንጫፉ ተገንጥሎ
ደርቆ ተንጠልጥሎ
እንዴት ሊኖር ነው ከዛፉ ተነጥሎ
ያለባህሪው ስር ሰዶ ተተክሎ፤

* * *

እናቴ «ተሰለም ተባረክ» ብላኝ
ለሰኔ ተክለኃይማኖት እንድሄድ ነግራኝ
ደብተራውም ቄሱም ዲያቆኑም አንድ ቢሆንብኝ
አልቆርብም ብዬ ወሰንኩኝ
የጥፈት ማተቡንም እላጠል ቆም አልኩኝ፤

* * *

ሳያሰፍረው መንሰፍሰፉ
በወገን ስም መወንጨፉ
መቀመጫ አገኘሁ ብሎ ሮጦ
ለሆዱ .. በሆዱ ተቀምጦ፤

* * *

**ማሳሰቢያ**

ይህ ፅሑፍ ስለታተመበት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኮምፒውተር ዘዴ ለማወቅ ለምትፈልጉ ሁሉ በሚከተለው አድራሻ ዳሸን እንጂነሪንግን መጠየቅ ትችላላችሁ፡—


DASHEN ENGINEERING COMPANY
39120 ARGONAUT WAY SUITE 161
FREMONT, CALIFORNIA 94538 U.S.A
Telephone: 415-791-1159 x161
or 408-270-0636 (Evenings)
Fax: 408-2700636